የተከበሩ ወላጅ/አሳዳጊ:

**ከየካቲት 2 እስከ መጋቢት 11** ቀን ልጅዎት የ እንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና /ELPA21 ቴስት ይወስዳል/ትወስዳለች:: ይህ ዓመታዊ ቴስት የተማሪዎትን የእንግሊዘኛ ቋንቋ የመስማት: የመናገር: የማንበብ እና የመጻፍ እድገትን አስመልክቶ መረጃ ይሰጣል:: በተጨማሪም የ ELPA21 ቴስት ተማሪዎት ምን ዓይነት የ እንግሊዘኛ ቋንቋ አገልግሎት እንደሚያስፈልገው/እንደሚያስፈልጋት በማሳወቅ ለት/ቤቱ ውሳኔ የሚረዳና እንዲሁም የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ተማሪዎች ለመናገር: ለማንበብ: ለመጻፍ: እና የእንግሊዘኛ ቋንቋን እንዲረዱ ከመደገፍ አኳያ በምን ያህል ደረጃ እየሰራ እንደሆነ መረጃ ይሰጣል::

ሁሉም ብቁ የሆኑ የ እንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች እንዲሁም ለፈተናው ብቁ ሆነው ወላጆቻቸው አገልግሎቱን እንዳያገኙ የወሰኑ ተማሪዎች በሙሉ ይህንን ቴስት ይወስዳሉ::

በተቻልዎት ሁሉ ቴስቱ በሚሰጥበት ጊዜ ልጅዎት በት/ቤት እንዲገኝ/ እንድትገኝ እንዲያደርጉልን እንጠይቃለን::

የ ELPA21 የቴስት ውጤት ይፋ እንደሆነ የልጅዎትን ፕሮፋይል እና አጠቃላይ የ እንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃቱን/ቷን ከእያንዳንዱ የመናገር: የመስማት: የማንበብ: እና የመጻፍ ውጤት ጋር በደብዳቤ እንዲደርስዎት ይደረጋል::

ልጅዎት ስኬታማ እንዲሆን/ እንድትሆን ከማረጋገጥ አኳያ ከኛ ጋር በመስራትዎ እናመሰግናለን::

ከማክበር ሰላምታ ጋር